# ፍካሬ ዜና

## ጥቅምት 5 ቀን 2010 ዓ ም

- *የወያኔው ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ስልጣን የለቀቀበትን ምክንያት ግልጽ አደረገ*
- *ተመስገን ደሳለኝ ተለቀቀ*
- *ወያኔ መብቶቻቸውን የጠየቁ የንፁሀን ዜጎችን ደም አፈሰሰ*
- *በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተሞች የህፃናት ነጋዴዎች ቁጥር እየበዛ መሆኑ ተገለጸ*
- *የብር ዋጋ መቀነስ የዋጋ ንረት እንደሚያስከትል ስጋት ማስፈኑ ታወቀ*
- *በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ወፍራም ደሞዝ የሚበሉ የወያኔ ሹመኞች ቁጥር በርካታ መሆኑ ተሰማ*
- *ወያኔ በቀሰቀሰውና ባራገበው ግጭት የተፈናቀሉ ወገኖች በርሀብና በበሽታ እየተሰቃዩ መሆኑ ተነገረ*
- *የወያኔ የሙስና ድራማ ፋይዳ ቢስ መሆኑ እያነጋገረ ነው ተባለ*
- *የባእዳን ኃይሎች የወያኔን የእድሜ ገመድ ለማራዘም እየዶለቱ መሆናቸው ታወቀ*
- *ቅዳሜ በሱማሊያ ውስጥ በፈነዳው ከባድ ፈንጅ የሞተውና የቆሰለው ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ተነገረ*

***<u>የወያኔው ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ስልጣን የለቀቀበትን ምክንያት ግልጽ አደረገ</u>***

- የወያኔው ምክር ቤት አፈጉባዔ ስልጣን የለቀቀበትን ምክንያቶች በትናንትናው ዕለት ለአንድ የኦሮሚኛ ቋንቋ የአገር ውስጥ ቴሌቪዥን ጣቢያ በሰጠው ቃለ ምልልስ ስልጣን የለቀቀበትን ምክንያት አቅርቧል;፡ "ተራራ የሚያክል ስልጣን ይዞ በመቀመጥ የሕዝብን ጥቅም ሲነካ ከማየት ይልቅ ማስተካከል ካልተቻለ ስልጣን ለቆ ከሕዝብ ጋር በመሆን መታገል መፍትሄ ስለሆነ ስልጣኔን ለቅቄያለሁ ብሏል፡፡ አባዱላ ለሕዝብ አስቦ ስልጣን መልቀቁና በእርግጥም ቃል የገባውን ማረጋገጥ የሚቻለው ወደፊት በተግባር በሚያሳየው እንቅስቃሴ ይሆናል በማለት ብዙዎች ይተቻሉ፡፡

***<u>ተመስገን ደሳለኝ ተለቀቀ</u>***

- ተመስገን ደሳለኝ እሑድ ጥቅምት 5 ቀን 2010 ዓ.ም. ከእስር የተፈታ መሆኑን ወንድምየው በፌስቡክ ካስተላለፈው መእልክት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የተፈረደበትን የሶስት ዓመት ቅጣት ጨርሶ መፈታት የነበረበት ባለፈው አርብ ሲሆን የወያኔ አገዛዝ ለምን እስከዛሬ እንዳስቀመጠው ግልጽ ምክንያት አልሰጠም፡፡ መፈተታ በነበረበት ቀን ባለመፈታቱ ተመስገን ደሳለኝ የረሃብ አድማ መጀመሩ በተነገረ በአንድ ቀን ውስጥ ሊፈታ ችሏል፡፡

***<u>ወያኔ መብቶቻቸውን የጠየቁ የንፁህን ዜጎችን ደም አፈሰሰ</u>***

- *ወያኔ ውስጥ ውስጡን ባደረገው ቅስቀሳ በሐረርጌ፣ በቦረና፣ በባሌ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ደም እንዲፈስ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ለጽኑ የአካል ጉዳተኝነት እንዲዳረጉና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከቄያቸው እንዲሰደዱ ምክንያት መሆኑን በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሰብአዊ መብቶት ተሟጋቾች ድርጅቶች እያስረዱ መሆናቸው የሚታወቅ ነው። ባሳለፍነው ሳምንት በአምቦ፣ በሻሸመኔ፣ በአቦምሳ፣ በወሊሶ፣ የወያኔን ደም አፍሳሽነት በማውገዝ ግዙፍ ሰላማዊ ሰልፎች ተካሂደዋል፡፡ በሻሸመኔ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ወያኔ በአልሞ ተኳሾችና በእሩምታ ተኩስ ወደ ሃያ የሚጠጉ የንፁህን ዜጎችን ደም ማፍሰሱ ታውቋል፡፡ በዚህ ወያኔ በወሰደው ጭፍጨፋ አንድ የሰባት አመት ህፃን ፣ አንድ የሰባ ሦስት አመት ሽማግሌ፣ አንድ በሥራ ላይ የነበረ ሾፌር፣ የሚገኙበትና በርካታ መንገደኛ ሴቶችና ወንዶች በጽኑ መቆሰላቸው ታውቋል፡፡ ይህንን የወያኔን ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ በመቃወም የሚካሄዱት ሰልፎች በመጪዎቹም ቀናት በበርካታ አካባቢዎች እንደሚቀጣጠሉ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከሚወጡ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡*

***<u>በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተሞች የህፃናት ነጋዴዎች ቁጥር እየበዛ መሆኑ ተገለጸ</u>***

- በኢትዮጵያ ትላልቅ በሚባሉ ከተሞች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህጻናት ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውና በየመንገድ ዳር በጫማ አሳማሪነት፣ በሱቅ-በደረቴነት፣ የክብደት ሚዛን በማስጠቀም፣ ወዘተ. ሥራዎች ተሰማርተው ከጠዋት እስከ ማታ በመንገድ ዳር ቆመውና ተቀምጠው ሲታዩ ወያኔ የለየለት ፀረ-ሕዝብ መሆኑን የሚሳይ ነው ተብሏል፡፡ ወያኔ በየአመቱ የትምህርት መጀመሪያ ወር በሆነው በመስከረም የሚያሰማው መፈክር "አንድም ህፃን ከትምህርት ገበታ አይነጠልም" የሚል ሲሆን ሀቁ ግን ከአራት አመት እስከ አስራ ሦስት አመት የሚደርሱ ህፃናት ለእለት ጉርሳቸው በየጎዳናው እየተንከራተቱ እንደሚውሉ በግልጽ ይታያል፡፡ በአዲስ አበባ በየመንገዶቹ ጥጋጥግ በእንዲህ ያሉ ሥራዎች ተሰማርተው የሚታዩት ህፃናት ከጋሞና ከወላይታ የመጡ ህፃናት መሆናቸውን ይህን ጉዳይ አስመልክተው ከተካሄዱ ጥናቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

***<u>የብር ዋጋ መቀነስ የዋጋ ንረት እንደሚያስከትል ስጋ ማስፈኑ ታወቀ</u>***

- ከአሁን ቀደም በፍኖተ በተደጋጋሚ የብርን የምንዛሪ ዋጋ መቀነስ አስመልክቶ የቀረቡ ዘገባዎች ባሳለፍነው ሳምንት መታወጁ ታውቋል፡፡ የዓለም የገንዘብ ድርጅት የብር የምንዛሪ ዋጋ እንዲወርድ ያደረገው ግፊት ውጤት መሆኑ የታወቀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የተደረገበት ሰበብ የሀገሪቱ የውጪ ንግድ በእጅጉ በመንኮታኮቱ መሆኑን ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች ያስረዳሉ፡፡ የወያኔ ብሔራዊ ባንክ በውጪ ምንዛሪ ጭራሹን በመራቆቱ ኤኮኖሚውን ለማንሰራራት በሚል የተወሰደ እርምጃ መሆኑን የሚስረዱ የመዋእለ-ንዋይ ጠበብቶች እንደሚሉት ይህ እርምጃ ምንም ዓይነት ማገገም እንደማያስከትል ያስረዳሉ፡፡ እንደ ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድረጅት ውትወታ በአሁኑ ወቅት

የብር ምንዛሪ ሲሆን የሚገባው ለአንድ የአሜሪካ ዶላር ከአርባ እስከ ሃምሳ ብር ሲሆን ይህ የተደረገው ማሻሻያ የውጪ ንግዱን እንደማያንሰራራው ከወዲሁ ሀሳባቸውን የሚሰነዝሩ በርካቶች ናቸው፡፡ ወያኔ ቀደም ሲል ለመንግስት ሠራተኞች ያደረገው የደሞዝ ጭማሪ የባዶ ወረቀት ጭማሪ መሆኑን ብዙዎች ያስረዳሉ፡፡ የገበያ መናርና የብር ግሽበት በቅርቡ የወያኔን የኤኮኖሚ አቅም እንደሚንጡት የሚጠበቅ ነው ተብሏል፡፡

__በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ወፍራም ደሞዝ የሚበሉ የወያኔ ሹመኞች ቁጥር በርካታ መሆኑ ተሰማ__

- ጥቂት የማይባሉ የወያኔ ሹሞች በሀሰት የትምህርት ማስረጃ ዲግሪዎች ቁልፍ የሆኑ የሙያ ክህሎት የሚጠይቁ ቦታዎች መቀመጣቸው ተጨባጩ ሥራ ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ እየታየ ነው ተብሏል፡፡ አብዛኛዎቹ እንኳንስ የሥራውን ባህርይና ሥራውን ሊያውቁት ቀርቶ የተሾሙበት ቦታ ምን ዓይነት ክህሎት እንደሚጠይቅ እንኳ በቅጡ የማያውቁ መሆናቸው በሰፊት እየተነገረ ነው፡፡ ይህ በሀሰት የትምህርት ማስረጃ ለሚሾሙ የወያኔ ካድሬዎች የትምህርት ማስረጃውን የሚዘጋጅላቸው እራሱ ወያኔ መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች ያጋልጣሉ፡፡ በዚህ የሀሰት የትምህርት ማስረጃ በመስጠት ወንጀል አንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች በፖለቲካ ትእዛዝ እየፈጸሙት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በየዩኒቨርሲቲዎችም የሀሰት የትምህርት መረጃ የያዙ መመህራን መገኘታቸው አንዱ ለትምህርቱ ማሽቆልቆል ምክንያት ነው ተብሏል፡፡

__ወያኔ በቀሰቀሰውና ባራገበው ግጭት የተፈናቀሉ ወገኖች በርሀብና በበሽታ እየተሰቃዩ መሆኑ ተነገረ__

ከሐረርጌ ከተለያዩ ቀበሌዎች ቤቶቻቸው በእሳት ጋይተው፣ ከብቶቻቸው ተነድተውባቸው ዘመድ አዝማዶቻቸው በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉባቸው ከቀያቸው ተሰደው በመጠለያዎች እንደታጎሩ የሚታወቅ ነው፡፡ ለእነዚህ ወገኖች በአግባቡ የምግብና የህክምና አገልግሎት እንደማያገኙ ሁኔታውን በቅርበት ከተከታተሉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከወላጆቻቸው የተነጠሉ ሕፃናትና ከልጆቻቸው የተለዩ ወላጆች በመከራ ውስጥ እንደሚገኙ እነዚሁ ወገኖች ያስረዳሉ፡፡ የተከሰተው ግጭት ሙሉ በሙሉ የተረጋጋ ባለመሆኑ እነዚህን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች ወደየቀያቸው መልሶ ለማቋቋም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚታሰብ እንዳልሆነ ችግሩን በቅርበት የታዘቡ ያስረዳሉ፡፡

__የወያኔ የሙስና ድራማ ፋይዳ ቢስ መሆኑ እያነጋገረ ነው ተባለ__

- ወያኔ በሙስና ላይ ዘመቻ መክፈቱን የሚለፍፈው ሕዝባዊ አመጽ ሲበረታና ይይዝ ይጨብጠው ሲያጣ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ በቅርቡ በሙስና መታሰራቸው ከተነገሩት ውስጥ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በወያኔ ቁንጮዎች ትእዛዝ እንዲለቀቁ የተደረጉ መኖራቸው የወያኔ የሙስና ዘመቻ የእቃ እቃ ጨዋታ መሆኑን የሚሳይ ነው ተብሏል፡፡ በተያያዘም፣ ከወያኔ ቡድን በከፍተኛ ሁኔታ ሀገርን እየዘረፈና ሕዝብ እየመዘበረ የሚገኘው በሳሞራ ዩኑስ የሚመራው የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች ቡድን እስከ ዛሬ ከመሀሉ አንድ እንኳ በሙስና የተወነጀለ አለመኖሩ የወያኔ

የሙስና ዘመቻ የውሀ ወቀጣ እምቦጭ እንደሚሉት ያለ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ሜቴክ የተባለው የወያኔ የዘረፋ ድርጅት ሀላፊ የሆነው ጄኔራል ተብዬው ክንፈ በወያኔ ውስጥ ከሚገኙ ሌቦች ዋነኛው አጭሉግ ሌባ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ ሳለ እስካሁን ከሳሞራ ጋር ዘብጥያ አለመውረዱ ወያኔ የሀገርን ማጅራት የሚመቱ ቀማኞች ቡድን ስብስብ መሆኑን ያሳያል ተብሏል፡፡

## የባእዳን ኃይሎች የወያኔን የእድሜ ገመድ ለማራዘም እየዶለቱ መሆናቸው ታወቀ

የባእዳን ኃይሎች በተለይም አሜሪካና ሸሪኮቿ ወያኔን በስልጣን ለማቆየት እየዶለቱ መሆናቸው ከአንዳንድ አፈትልከው ከሚወጡ ድብቅ ሚስጥሮች መገንብ ተችሏል፡፡ በቅርቡ በወያኔ ላይ ማእቀብ ለመጣል የሚያስችል ረቂቅ ህግ ለአሜሪካው ኮንግረስ ለውሳኔ የሚቀርብበት ጊዜ መራዘሙ ወያኔ በሶማሌ ያዘመተውን ጦር እንደሚያወጣና በፀረ-አሸባሪነት ዘመቻ ተባቢሪነቱን እንደሚያቆም በመግለጹ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የዚህ ትርጉም ወያኔ እራሱን በእራሱ አሸባሪ ለማድረግ መወሰኑን በማያወላውል ቋንቋ ያስረዳል የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ካለመረዳት ይሁን በሌላ ወያኔ "የጥምር መንግስት" የተባለ አፍዝ አደንግዝ እንዲመሰርት በተመከረው መሰረት በ2012 ዓ.ም. ለሚካደው ምርጫ የወያኔ አጋሰስ የሆኑ ድርጅቶችን ለማካተት እንደታሰበ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለዚህ ይመስላል አንዳንድ የይስሙላ ተቃዋሚዎች ወያኔን ያካተተ የሽግግር መንግስት ምስረታ ሲሉ የሚደመጡት፡፡ የፖለቲካ አዋቂዎች እንደሚያስረዱት ወያኔን አካቶ መሸጋገር የሚባል ጉዳይ የእንቧይ ካብ ነው ተብሏል፡፡

## ቅዳሜ በሱማሊያ ውስጥ በፈነዳው ከባድ ፈንጅ የሞተውና የቆሰለው ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ተነገረ

- ቅዳሜ ጥቅምት 4 ቀን በሶማሊያ በፈነዳው ግዙፍ ፈንጅ እስካሁን ድረስ 189 ሰዎች መሞታቸው እና ከ 200 በላይ መቁሰላቸው ባለስልጣኖች ተናገረዋል። በአሁኑ ወቅት ተጎጅዎችን ከፍርስራሽ ውስጥ የማውጣት ስራ እየተካሄደ ሲሆን የሟቾቹ ቁጥር ከዚህ ከፍ ሊል እንደሚችል ተገምቷል። ሆስፒታሎች በተጎዱ ሰዎች የተጨናነቁ ሲሆን የአንዳንዶቹ ተጎጅዎችን መልክ ለመለየት አስቸጋሪ ሆኗል ተብሏል። የሶስት ቀናት ብሔራዊ ሀዘን የታወጀ ሲሆን ሕዝቡም ደም እንዲሰጥ ተጠይቋል።